# በ 2009-2012 ለሚመረቁ ተማሪዎች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

## Graduation Requirements for the Class of 2009-2012

የአካዳሚክ አችቭመንት ሰርቲፊኪት ለማግኘት (CAA)

የአካዳሚክ አችቭመንት ሰርቲፊኬት ለማግኘት ሁሉንም በስቴትና በትምህርት ቤቶች አስተዳደር(ዲስትሪክት) አማካይነት የተደነገጉትን[1] ማሟላት ያስፈልጋል። ይህም የማጠናቀቂያ ፕሮጀክቶች(ከልሚኔቲንግ ፕሮጀክት) እና ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ ባሻገር ፕላን የተሰኙትን ይጨምራል እንዲሁም ፤

(1) የዋስልን የንባብና የጽሁፍ ፈተና ክፍሎች ማለፍ ወይም

የዋስልን ፈተና ካላለፉ የተፈቀዱ የንባብና የጽሁፍ አማራጮችን ማለፍ ይህም የሚቀጥሉትን ያካትታል፤

a. ንባብ :

i. ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን የከፍተኛ ትምህርት ምደባ ፈተናዎችን(AP) 3 ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ማምጣት ይኖርባቸዋል። የእንግሊዝኛ ሊትሪቸርና አጻጻፍ(ኢንግሊሽ ሊትሪቸርና ኮምፖዚሽን) ፤ማክሮኢኮኖሚክስ፤ማይክሮኢኮኖሚክስ፤ሳይኮሎጂ፤ዩናይት ስቴስት ሂስትሪ፤ ዎርልድ ሂስትሪ፤ዩናይትድ ስቴትስ ጋቨርመንት ኤንድ ፖለቲክስ፤ኮምፓራቲቭ ጋቨርመንት ኤንድ ፖለቲክስ ወይም

ii. በተማሪዎች የትምህርት መለኪያ ኤስ.ኤ.ቲ(SAT) እና ኢ.ክ.ት( ACT) የንባብ ነጥብ አነስተኛውን ነጥብ ማምጣት። ይህ በዋሽንግተን ስቴት የትምህርት ቦርድ በኩል በጥር(ዲሰምበር) 1, 2007 ባላለፈ ጊዜ በይፋ የሚገለጽ ነው።

b. መጻፍ:

i. የከፍተኛ ምደባ ፈተና(አድቫንስድ ፕሌስመንት)በእንግሊዝኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ 3 ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ካመጡ ወይም

ii. በኤስ.ኤ.ቲ(SAT) የተሰኘ የችሎታ መለኪያ እና ኢ.ክ.ት( ACT) የጽሁፍ ፈተናዎች አነስተኛውን ነጥብ ካመጡ። ይህ የፈተና ውጤት በዋሽንግተን ስቴት የትምህርት ቦርድ በዲሰምበት 1, 2007 ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይፋ ይደረጋል።

እንዲሁም

(2) የዋልን የሂሳብ ፈተና ማለፍ ወይም

የዋስልን ፈተና ካላለፉ በሂሳብ ምትክ የሚሰጠውን ሌላ የተፈቀደ የሂሳብ ፈተናን ማለፍ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል ፤

a. በ ኢ.ክ.ት.( ACT,) የሂሳብ ፈተና 19 ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ማምጣት፤

b. በከፍተኛ ትምህርት ምደባ(AP) ፈተናዎች በካልኩለስና ወይም ስታትስቲክስ 3 ወይም ከዚያ በላይ ማምጣት

c. በ ኤስ.ኤ.ቲ( SAT )የሂሳብ ፈተናዎች 470 ወይም ከዚያ በላይ ማምጣት

---

[1] የስቴት የትምህርት ቤት ቦርድ ሁሉም ተማሪዎች ለመመረቅ የሚያስፈልጋቸውን የሂሳብ ነጥቦች ከሁለት ወደ ሶስት ከፍ ለማድረግ ሃሳብ አለው። ይህ ደግሞ ተማሪው ስድስት የሂሳብ ክፍሎችን ከ 9ኛ፣ 10ኛና 11ኛ የክፍል ደረጃ ከሚጠበቀው እውቀት ጋር የተዛመደ ትምህርት ያስፈልገዋል ማለት ነው። (GLEs).

ወይም

(1) የዋስልን ፈተና ሳያልፉ ቀርተው ነገር ግን ከዋስል/የክፍል ውጤት ጋር በማነጻጸር( WASL/Grades Comparison) የተማሪው የሂሳብና ወይም የእንግሊዝኛ ትምህርት ውጤት ተመሳሳይ ትምህርት ከወሰዱና የዋስልን ፈተና ካለፉ ተማሪዎች ጋር በማስተያየት። ይህ አማራጭ ለ12 ክፍል ተማሪዎችና በአጠቃላይ ነጥባቸው(ግሬድ ፖይንስ አቨሬጅ) ቢያንስ 3.2 ለሆኑት ብቻ ነው።

(2) የዋስልን ፈተና ያላለፉና ነገር ግን የስራ ውጤቶችን በመሰባሰብ ነጥብ እንዲሰጣቸው ለስቴቱ ማቅረብ( ማስረጃ ሰባስቦ ማቅረብ)

ዲፕሎማን ስለ ማግኘት

የአካዳሚክ አችቭመንት ሰርቲፊኬት ለማግኘት ማሟላት ያለባቸውን ያሟሉ ተማሪዎች ሆነው ነገር ግን በዋስል የሚሰጠውን የሂሳብ ፈተና ወይም ሌላ ይህን የሚተካ የተፈቀደ አማራጭን ለማለፍ ያልቻሉ ሁለት የሂሳብ ትምህርት ወይም ሲቲኢ( CTE) ተመጣጣኝ ነጥብ(አራት የትምህርት አይነቶች) በመውሰድና የዋስልን ፈተና እንደገና በመውሰድ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ በመውሰድ መመረቅ ይችላሉ።

ተማሪው የዋስልን ፈተና በሚወስድበት ጊዜ የሂሳቡን ፈተና ካለፈ እሱን ለመተካት ሲወስዱት የነበረውን የሂሳብ ሆነ ተመጣጣኝ የትምህርት አይነቶች መማራቸውን ማቋረጥ ይችላሉ። ከዲፕሎማ ይልቅ ሰርቲፊኬት ኦፍ አካዳሚክ አችቭመንትን ያገኛሉ።

የግል ሰርቲፊኬት ኦፍ አችቭመንት ስለማግኘት (CIA)

የግል ሰርቲፊኬት ኦፍ አችቭመንት የሚሰጠው የልዩ ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች ሆነው የዋስልን ፈተና (በማመቻቸትም ሆነ ባለመመቻቸት) መውሰድ የማይችሉ ነገር ግን በስቴትና በትምህርት ቤት አስተዳደር በኩሉ የተዘጋጁትን መስፈርቶች ላሟሉ ነው። እንዲሁም

(1) በ 9ነኛ ወይም 10ኛ ክፍል የተመቻቸ ዋስል( WASL-Modified (WASL-MO) ) ወይም WAAS የተሰኘ ፖርትፎልዮ ካሟሉ ወይም

(2) ለእድገታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ዋስል (Developmentally Appropriate WASL (WASS-DAW) ) በ11ኛ እና በ 12ኛ ክፍል ከወሰዱ

መማራቸውን የሚመሰክር ሰርቲፊኬት (ሰርቲፊኬት ኦፍ አቴንዳንስ)

የልዩ ትምህርት ተማሪዎች ሆነው ነገር ግን ሰርቲፊኬት ኦፍ ኢንዲቭዥዋል አቴንዳንስ ለማግኘት የሚጠበቀውን መስፈርት ለማሟላት ያልቻሉ አስተዳደሩ ሰርቲፊኬት ኦፍ አቴንዳንስ ሊሰጣቸው ይችላል። "ኬቪንስ" በተሰኘው ህግ መሰረት አስተዳደሩ ለሁሉም የልዩ ትምህርት ፕሮግራም ተማሪዎች ሆነው ቀጣይ ልዩ ትምህርት መውሰዳቸውን የሚገልጽ የግል የትምህርት ፕሮግራም የሚሰጣቸው ወይም ከዚሁ ጋር የተዛመዱ አግልግሎቶች የሚሰጣቸው እድሜአቸው ከ 18 እስከ 21 የ ሆኑ (መስፈርቶቹንም ያላሟሉ ቢሆንም እንኳ) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአራተኛው አመታቸው[2] በምረቃው ስነ ስርአት እንዲሳተፉ ይፈቅዳል። ተማሪዎች የግል ትምህርት ፕላን እቅዳቸውን( IEP) በሚያሟሉበት ወይም 21 አመት ሲሞላቸው በ ምረቃው ግዜ ለመሳተፍና ሰርቲፊኬት ኦፍ አቴንዳንስ ለመውሰድ መምረጥ ይችላሉ።

---

[2] ልዩ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ከዚያ በኃላ በየአመቱ በምረቃ ስነ ስርአት ለመሳተፍ አይችሉም። ነገር ግን በሁለተኛ ደረጃ የአራተኛ አመት ጊዜአቸው በኃላ ለግል ሰርቲፊኬት ኦፍ አችቭመንት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸውን ካሟሉ እንደገና በምረቃ ወቅት ለመመረቅ ይችላሉ።